# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል
## 23 ኛ ሳምንት
## ጌታችን ኢየሱስ በደብረ ዘይት

**ዓላማ**
- ❖ ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት መማርና ችግረኞችን መርዳት ስለሚገኝ ጥቅም መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**
- ❖ *"ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት"* ማቴ. 25÷40

**ምንባብ**
- ❖ ማቴ.25÷31-46

**መግቢያ**
- ❖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደብረዘይት በተባለው ተራራ የተለያዩ ትምህርቶችን አስተምሮአል።
- ❖ ዛሬም ከእነዚህ ትምህርቶች ስለዳግም ምጽአቱ እና ስለ ፍርድ ቀን ያስተማረውን እንማራለን።

**ትምህርቱ**
- ❖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ በዓለም መጨረሻ ለፍርድ ሲመጣ የሚሆነውን ነገራቸው።
- ❖ በዚህ ትምህርቱም በክብር እንደሚመጣ፤ በፍርድ ወንበር በመላእክቱ ታጅቦ እንደሚቀመጥና እንደሚገለጽ አስተማራቸው።የዓለም ሕዝቦች በሙሉ ተሰብስበውም÷ ጻድቃን በቀኙ ኃጥአንም በግራው እንደሚያስቆም እንደሚለይም አስተማራቸው።
- ❖ በቀኙ ለቆሙትም *"እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና። ....እውነት እላችኋላሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ ስንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።"*
- ❖ በግራው ያሉትንም ደግሞ *"እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ሂዱ።ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፣እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና... እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።"*
- ❖ ስለዚህ ጌታችን *"ኃጥአን ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።"* አለ።
- ❖ ችግረኞችን ስንረዳም ጌታችን እርሱን እንደረዳነው ይቆጥረዋል።እናም ልብስ፣ ምግብ ወይም ሌላ መሠረታዊ ፍላጎታቸው ላልተሞላላቸው ርኅራኄ ሊኖረን ልንረዳቸውም ይገባል። እንዲህ በማድረጋችንም *"እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።"* ይለናል።

**ጥያቄ**

1.ክርስቶስ ስለዳግም ምጽአቱ የት አስተማረ?
2.ለፍርድ አመጣጡ እንዴት ነው?
3.ጌታችን ለፍርድ ሲመጣ በቀኝና በግራ የሚቆሙት ማን ናቸው? ምንስ ይላቸዋል?

**ደብረዘይት**
- ❖ በተራራው በብዛት በሚገኘውና ዘይት/ቅባት ባለው ዛፍ ምክንያት ደብረዘይት ተብሎል።ጌታችን በደብረዘይት ስለ ዳግም ምጽአቱ አስተምሮል።
- ❖ ቤተክርስቲያናችንም ይሄን ትምህርት መሠረት አድርጋ የጌታችንን ዳግም ምጽአት ታስባለች።
- ❖ ይህ ሳምንት ከእሁድ ጀምሮ ደብረዘይት፣እኩለ ጾም ይባላል።

**መዝሙር**

በደብረ (2) ዘይት ምሥጢረ ምጽአቱን
የገለጸበት በደብረ(2) ዘይት

ይቆየን።